## የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) የአመራር ምክር ቤት መደበኛ ጉባኤውን አካሄደ።

## የወቅቱን ሁኔታ ገምግሞ፣ የጋራ ትግሉን ለማጠናከር ተጨማሪ መመሪያ ሰጠ።

የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) የአመራር ምክር ቤት ቅዳሜ ጥር 28፣ 20008 (Feburuary 6, 2016) መደበኛ ጉባኤውን አካሂዷል። በዚህ ጉባኤው ምክርቤቱ ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበትን ሁኔታ፣ በህዝባችን ትግል አኳያ የሚታዩትን ተስፋ ሰጭ ገጽታዎችና አሳሳቢ ክስተቶችን በሰፊው ገምግሟል። የሸንጎ የተለያዩ የስራክፍሎች የሚያካሂዱትን ተግባር በተመለከተ የቀረቡትን የስራ ዘገባዎች መርምሯል፡፡ በመቀጠልም በህዝበችን ላይ እየደረሰ የሚገኘውን ግፍ ሊያከትም እንዲችልም መካሄድ በሚገባው ትግል ላይ አስፈላጊውን የተግባር መመሪያዎች ሰጥቷል፤ የትግል ጥሪም አስተላልፏል።

የ25 ዓመቱ የህወሀት/ኢህአዴግ የአምባገነን የግፍ ስርአት ኢትዮጵያን አደጋ ላይ ጥሏል። ኢትዮጵያውያንን አስመርሯል። በሁሉም የሀገራችን ክፍል የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ህገ መንግስታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እውን የሚሆንበትን ጊዜ ናፍቋል። መናፈቅ ብቻም ሳይሆን፣ አንድነቷ በተጠበቀ ኢትዮጵያ ስር መብቱን ለማሰከበር፣ የህግ የበላይነትን እውን ለማድረግ፣ ከፋፋይ ስርአትን ለማስወገድ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በየቦታው ተቃውሞውን በተለያየ መልክ በመግለጥ ላይ ይገኛል። ህዝባችን በተለያየየ ሀገሪቱ ክፍል መብቱን ለማስከበር ከፍተኛ መስዋእትነትን በመክፈል ላይ ነው። ስርአቱ በመፍረክረክ ላይ ይገኛል። ክንዱ ዝሏል። አደንቋሪ ፕሮፓጋንዳውን የሚያዳምጠው ጆሮ አጥቷል። በሀገራችን ውስጥ ያለው ሁኔታ የሚያሳየው ሀገራችን የለውጥ ዋዜማ ላይ መሆኗን ነው።

በዚህ አኳያ በአሁኑ ሰአት በመላ ሀገራችን በተለይም ደግሞ አሮሚያ፤ አማራና ጋምቤላ ተብለው በሚታወቁት ክልሎች እየተካሄደ ያለውን የመሰረታዊ መብቶች መገፈፍን፤ የመሬት ቅርምትንና ዘረፋን፣ ዳር ድንበርን ማስደፈርን፣ አግላይ የሆነን ፖለቲካና ህዝብን ከህዝብ የማጋጨት ተግባር የመቃወም ትግልና ህዝባዊ እምብተኛነት ሸንጎው ከዚህ በፊት ደጋግሞ እንዳደረገው ሁሉ አሁንም በጽኑ ይደግፋል። መራራውን ጭቆናና ግፍ ባልተቋረጠ መልክ በህዝብ ላይ የጫነውን አገዛዝ በማስወገድ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትንና በእኩልነት ላይ የተመሰረተን አንድነት ለመመስረት ትግል ከሚያደርጉ ሁሉ ጋር የትግል አጋርነቱን ይገልጻል።

ስርአቱ ለዚህ የህዝብ ትግል ተገቢ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ እንደተለመደው በማን አለብኝነት ለማፈን የሚወስደውን የሀይል እርምጃ፣ እስራት፣ ድብደባና ግድያ ምክር ቤቱ ያወግዛል። በደል ለደረሰባቸው ሁሉም የሀዘናቸው ተካፋይነቱን ይገልጣል። ከዚህ ሁኔታ ጋር ተያይዞም የታሰሩት ሁሉ ባስቸኳይ እንዲለቀቁ፣ ንብረታቸው ለጠፋው እንዲሁም በስርአቱ የጸጥታ ሀይሎች ለተገደሉ አስፈላጊው ህጋዊ ካሳ ለቤተሰቦቻቸው እንዲከፈልና ገዳዮቹም ሆኑ ትእዛዝ ሰጭዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ለማድረግ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ትግሉን እንዲቀጥል ምክር ቤቱ ጥሪ አቅርቧል።

ከዚህ ጋር በተያያዘም ይህን የህዝብ ትግል ለጠባብና ከፋፋይ አላማ ሊያውሉት የሚጥሩትን አንዳንድ የውስጥም የውጭም ሀይሎች እንዲሁም የስርአቱን ደባ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በጥንቃቄ ነቅቶ እንዲከታተልና የከፋፋዮች ሰለባ እንዳይሆንም ነቅቶ እንዲጠብቅ አሳስቧል።

የህዝባችንን የትግል መነሳሳት ወደተፈለገው የስርአት ለውጥ እንዲያመራ የተቃዋሚው ወገን ታላቅ ሀላፊነት እንዳለበትና በተናጠል የሚደረግ ትግል ለስርአቱ እድሜ መራዘም የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በመገንዘብ ይህን ሁኔታ ለመቀየር የሚያስችል አስተማማኝና ቀጣይ ትግል ለማካሄድ ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመስራት በሸንጎው በኩል የሚደረገውን ጥረት ከመረመረ በኋላ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮና ቅድሚያ ተሰጥቶት አንዲቀጥል፣ ሌሎች የአንድነት ሀይሎችም የጋራ ትግሉን እውን ማድረግ አጣዳፊነት ተረድተው ጠንካራ የተቃዋሚ ህብረት በመመስረቱ ተግባር ላይ በጋራ መረባረብ ይገባቸዋል ሲል ምክር ቤቱ ለሁሉም የአንድነት ሀይሎች የትብብር ጥሪውን በድጋሜ አስተላልፏል።

የህወሀት/ ኢህአዴግ አምባገነን ስርአት ዕለታዊ ተግባር በሀገሪቱ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት እንዲጠፋ እያደረገ እንደሆነ አለም አቀፍ ህብረተሰቡ ተገንዝቦ ይህን አደጋ ለማስወገድም የኢትዮጵያ ህዝብ ለመሰረታዊ መብቱ መከበርና ፣ ለህግ የበላይነት የሚያካሂደውን ትግል እንዲያግዝ ከምን ጊዜውም የላቀ ዲፕሎማሲያዊ ትግል እንዲካሄድ ምክር ቤቱ ተጨማሪ መመሪያ ሰጥቷል።

በመጨረሻም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለመሰረታዊ ጥያቄዎቹ መልስ ማግኘት ማለትም ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር፣ ራሱ የመረጠውና የሚቆጣጠረው መንግስት ለመመስረት፣ ለህግ የበላይነት መከበር፣ የከፋፋይ ስርአት እንዲያከትም የፖለቲካ ስርአቱ ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ ተሳታፊ የመሆን መብቱ እንዲከበር፣ በነጻነትና ያለፍርሃች መኖር እንዲችል የኢኮኖሚ ተስፋ፣ የማህበራዊ ፍትህ ፣ እውን እንዲሆን ሁሉም ዜጋ ማንነቱ ተከበብሮ በቋንቋው የመጠቀም፣ ባህሉን የማዳበር፣ መብቱ ተጠብቆ መኖር…ወዘተ እንዲችል ለሚደረገው ትግል ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትግል አጋርነቱን እንዲገልጥ የአንዱ ኢትዮጵያዊ መጠቃት የሌላው መጠቃት እንደሆነ በመገንዘብ እጅ ለእጅ በመያያዝ በተባበረ ትግል የጭቆናውን ስርአት ለማስወገድና ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት የሚያሰተናግድ ህገ-መንግስታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመመስረት በጋራና በመተጋገዝ እንዲታገል የሸንጎው የአመራር ምክር ቤት ጥሪ አድርጓል።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : **shengo.derbiaber@gmail.com**